ከሰኔ 30 በበኋላ የዋሽንግተን ግዛት አብዛኛዎቹን የከኮቪድ-19 ገደቦችን ያነሳል። የዋሽንግተን ሃገር አስተዳዳሪ ጄይ ኢንስሊ ወደ መደበኛው ስራ ለመመለስ ለነዋሪዎች ባወጣው ገደብ መሰረት ከአስራ ስድስት እና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያላቸው የክልሉ ነዋሪዎች ሰባ ከመቶው ቢያንስ አንድ ክትባት ማግኘት አለባቸው ።

በተጨማሪም ከአሥራ ስድስት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የኪንግ ካውንቲ ነዋሪዎች ከ70% በላይ ሙሉ በሙሉ ክትባት ወስደዋል ይሄም ማህበረሰቡ በከፍተኛ ደረጃ ጤናውን እንዲጠብቅ ይረዳል።

የኮቪድ-19 በሽታ ፈፅሞ አልጠፋም ይልቁንም የተለያዩ ተለዋዋጭ እና እጅግ ተላላፊ ዓይነቶችን በመፍጠር ስርጭቱን ቀጥሏል። ስለዚህ ገና ያልተከተቡ ወይም መከተብ የማይችሉትን ሰዎች ለመጠበቅ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ኪንግ ካውንቲ ለሁሉም ዘር እና የቤህር ቡድኖች ወይም ክልሎች 70% ያህል ክትባትቱን እስኪወስዱ ለማድረግ በፅናት እየሞከረ ነው። ስራችን ገና አልተጠናቀቀም። ተንቀሳቃሽ የክትባት አገልግሎትን በመስጠት ፣ በስራ ቦታ የሚደረጉ የክትባት ጥረቶችን በመደገፍ እና በማህበረሰባዊ መሰረት የሚደረጉትን ስልቶች በመደገፍ ክፍተቶችን ለማጥበብ ትኩረት ማድረጋችንን እንቀጥላለን።

## በሰኔ 30 የሚነሱት የትኞቹ ገደቦች ናቸው?

እንደ ምግብ ቤቶች ፣ የሸቀጥ መደብሮች ፣ ሱቆች ፣ ቲያትር ቤቶች ፣ እና ቤተ-መዘክሮች ላሉ የንግድ ቦታዎች ወይም የህዝብ ስፍራዎች ላይ መገኘት የሚገባቸውን የሰዎች ብዛት የሚወስን ገደብ የለም ። እንዲሁም የማህበራዊ ርቀትን የመጠበቅ ግዴታ ቀርቷል። ሆኖም የግለሰብ የንግድ ባለቤቶች እነዚህን ገደቦች በራሳቸው መርጠው ለመጠበቅ ይችላሉ።

## የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብሎችን በአደባባይ/ህዝብ በሚሰበሰብበት ስፍራ ላይ አሁንም መጠቀም ይኖርብኛል?

ከቤት ሲወጡ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ከእርስዎ ጋር መያዙ ጠቃሚ ይሆናል።

- በግዛቱ መመሪያ መሰረት ፤ ክትባት ያልተከተቡ ወይም በከፊል የተከተቡ ሰዎች በቤት ውስጥ የህዝብ መገልገያ ስፍራ ቦታዎች ላይ ሲገቡ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ማድረጋቸውን መቀጠል አለባቸው።
- ክትባቱን ሙሉ በሙሉ የተከተቡ ሰዎች በአብዛኛው የህዝብ መገኛ ቦታዎች ውስጥ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል አለማድረግ ይችላሉ።
- የንግድ ስራ ቦታዎች ደንበኞቻቸውንና ሰራተኞቻቸውን የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል እንዲያደርጉ መጠየቅ ወይም ማስገደድ ይችላሉ።
- ማንኛውም ሰው እንደ ሆስፒታል እና ሌሎች የጤና ጥበቃ ቦታዎች ላይ የማረሚያ ቤቶች ላይ፣ ቤት የሌላቸው ሰዎች መጠለያ ቦታዎች ላይ፣ ትምህርት ቤቶች እና የህፃናት እንክብካቤ ቦታዎች ላይ እና የህዝብ ማመላለሻ ትራንስፖርት ላይ የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል መልበስ አለበት። የረጅም ጊዜ እንክብካቤ ማቆያ ቦታዎች በተናጥል መመሪያ መስራታቸውን ይቀጥላሉ።

## ወደ ንግድ ስፍራችን ወይም ወደ ድርጅታችን ለሚመጡ ሰዎች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ማድረግ እንዲቀጥሉ ማስገደድ እንችላለን?

አዎን፤ ማንኛውም የንግድ ሰራተኛ ወይም ድርጅት ሰዎችን የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል እንዲያደርጉ ማስገደድ ይችላል። ነገር ግን የግዛቱ የጤና ደንብ/ትእዛዝ ስለ ፊት መሸፈኛዎች በወጣው ደንብ መሰረት ነጋዴዎች ወይም ድርጅቶች ለአካለ ጉዳተኛ ሰዎች በሚቻላቸው መጠን አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላት አለባቸው። የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ህፃናትን ፤የጤና ችግር ያለባቸውን ሰዎች እና ክትባት ያልተከተቡ ሰዎችን ከኮቪድ-19 ይከላከላል። በተጨማሪም ክትባት ለተከተቡ ሰዎች ደግሞ ተጨማሪ የጥንቃቄ ዋስትና ይሆንላቸዋል።

## የንግድ ሥራዬ ላይ ወይም የሥራ ቦታዬ ላይ የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ የሚየስችሉኝ ምን ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ እችላለሁ?

ሰራተኞችን ፣ ደንበኞችን እና ጎብኚዎችን ለመጠበቅ አንዳንድ የመከላከያ እርምጃዎች ግዴታ ባይሆኑም የተወሰኑ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መከተል አስፈላጊ ነው። ኮቪድ-19 አሁንም ከእኛ ጋር ነው። ቫይረሱም በአየር ላይ ይሰራጫል።

- ክትባቱን ያልተከተቡ ሰራተኞችና ደንበኞች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- የአፍና የአፍንጫ ሽፈኛ ጭንብልን መጠቀም ተቀባይነት ያለው የስራ አካባቢ /ሁኔታ ፍጠር (አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ)
- በቤት ዉስጥ በቂ እና ንፁህ አየር የሚዘዋወርበትን መንገድ ማሻሻል (በቤት ዉስጥ የንፁህ አየር ዝውውርን ማሻሻል የሚረዳ መመሪያ ይመልከቱ)
- ሰራተኞች ክትባት እንዲወስዱ እና በተፈለገው ሰዓት የኮቪድ ምርመራ እንዲያደርጉ ያበረታቱ:: ሰራተኞች በሚሰሩበት ቦታ ክትባት እንዲወስዱ መንገድ ያዘጋጁ::
- አመቺ ሲሆን ስብሰባዎችን ከቤት ዉጪ እንዲደረጉ ማበረታታዎትን ይቀጥሉ።

እንደተለመደው ሁሉ እጅን በተገቢው ሁኔታ መታጠብ የተላላፊ በሽታዎችን ስርጭት ለመከላከል ጥሩ መንገድ ነው።

## የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል የማያደርጉ ሰዎችን ወደ ንግድ ስራዬ ወይም የስራ ቦታዬ እንዲገቡ መፍቀድ እችላለሁ?

በጤና መምሪያ ቢሮ መሠረት፥ የንግድ ስራዎች እና ድርጅቶች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብልን ማድረግ በተመለከተ አማራጮች አሏቸው። የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ያላደረጉ ሰዎችን ሙሉ በሙሉ ክትባቱን እንደወሰዱ መገመት
- ግዴታ ባይሆንም የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ያላደረጉ ደንበኞችን እና ጎብኚዎችን የኮቪድ-19 ክትባት መከተባቸውን ማረጋገጫ መጠየቅ
- የክትባታቸው ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ማንኛውንም ሰው የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል እንዲያደርጉ መጠየቅ

የቤት ውስጥ የህዝብ ቦታዎች ያላቸው የንግድ ስራዎች እና ድርጅቶች መመሪያዎቻቸውን የሚያሳዩ ምልክቶችን መለጠፍ እና ክትባት ያልተከተቡ ሰዎች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ማድረጉን እንዲቀጥሉ ማስታወስ ይኖርባቸዋል።

## ደንበኞችንና ሰራተኞችን የኮቪድ-19 ክትባት መከተባቸውን ማረጋገጫ እዲያሳዩ መጠየቅ እችላለሁ?

አዎን፤ ነገር ግን ለአካል ጉዳተኛ ወይም ክትባት ሊከተቡ ለማይችሉ ሰዎች በሚቻልዎትን አስፈላጊ ነገሮች ማሟላት አለብዎት። እንደ የዋሽንግተን የስራና ኢንደስትሪ መመሪያ መሰረት፤ አሰሪዎች ሙሉ በሙሉ የተከተቡትን ሰራተኞች የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል ሳይለብሱ እንዲሰሩ ለመፍቀድ እቅድ ካላቸው፤ ሰራተኞቹን የኮቪድ 19 ክትባት መከተባቸውን ማረጋገጫ ማሳየት ይኖርባቸዋል።

ተቀባይነት ያለቸው ሰነዶች የሚከተሉትን ያካትታል፤

- የሲዲሲ ክትባት ካርድ
- የክትባቱን ካርድ የሚያሳይ ፎቶ
- ከጤና ጥበቃ የሚሰጥ የሰነድ ማረጋገጫ
- ከሰራተኛው ወይም ደንበኛው በፊርማ የተረጋገጠ መግለጫ

## እኔ ምግብ ቤት አለኝ ፤ በንግድ ስራዬ ላይ ተግባራዊ የሚሆን ልዩ ገደብ ይኖር ይሆን?

የለም፤ ለምግብ ቤት የወጣው መስፈርቶች ለሌሎች የችርቻሮ መቋቋሚያዎች ከወጣው ጋር አንድ ዓይነት ነው።

## በሃይማኖት ድርጅቶች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ልዩ ገደቦች አሉ?

የለም፤ ለእምነት ተቋማት የወጡት መስፈርቶች ከሌሎች የንግድ ስራዎች እና ድርጅቶች ጋር አንድ ዓይነት ነው። እንዴት በጥንቃቄ እንደገና እንደሚከፈቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በእምነት ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶቻችንን ገጽ ይመልከቱ።

## በትላልቅ ኮንሰርቶች እና የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ልዩ ገደብ ይኖር ይሆን?

በቤት ውስጥ ለሚከናወኑ ከ10,000 ሰዎች በላይ ለሚያሳትፉ ዝግጅቶች ከሚይዙት አቅም 75 በመቶ ብቻ እንዲጠቀሙ ተወስኗል። ነገር ግን የሚገቡትን ሰዎች ሁሉ የኮቪድ-19 ክትባት መከተባቸውን ማረጋገጫ እዲያሳዩ ከጠየቁ፤ ምንም ዓይነት የአቅም ገደብ የለም። ማህበራዊ ርቀት የመጠበቅ መስፈርቶች ባይኖሩም ታዳሚዎች የወቅቱን የአፍና የአፍንጫመሸፈኛ ጭንብል የማድረግ መስፈርቶችን መከተል አለባቸው።

## በሲኒማ ቤቶች፣ በቤተ-መዘክር እና በባህላዊ ዝግጅቶች ላይስ ተግባራዊ የሚሆኑ ገደቦች ይኖሩ ይሆን?

የመሰብሰቢያ ቦታዎች አቅምና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶች ለደንበኞች እና ለጎብኚዎች ተወግደዋል፣ ነገር ግን ክትባቱን ያልወሰዱ ሰዎች የአፍና የአፍንጫመሸፈኛ ጭንብል ማድረጉን መቀጠል ይኖርባቸዋል።

## የንግድ ስራዎች ፣ድርጅቶች እና ትላልቅ ቦታዎች የተከተቡ እና ያልተከተቡ ሰዎች የሚለዩበት ስፍራዎች ሊኖራቸው ይችላልን?

ሁሉም ድርጅቶች አገልግሎት በሚሰጡበት ስፍራ የተከተቡትንና ያልተከተቡን የሚለዩበት ክፍሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸዋል። ከ10,000 እና በላይ ሰዎችን ለሚያሳትፉ ትልቅ የቤት ውስጥ ዝግጅት ፤ ክትባቱን ለተከተቡ ሰዎች የሚያገለግል ክፍሎች ማዘጋጀታቸው ከሚይዙት አቅም 75 በመቶ በላይ እንዲይዙ አይፈቀድላቸውም። (ለምሳሌ፤ ላልተከተቡት የሚውሉ ክፍሎችን 75 በመቶ አቅም እንዲይዙ እና ለተከተቡት ደግሞ የሚይዙትን አቅም 100% ማድረግ አይቻልም)።

ማንኛውም ድርጅት የተከተቡና ያልተከተቡትን የሚለይ ክፍሎች ማዘጋጀት ከፈለገ ፤ የኮቪድ-19 የመሰራጨት አደጋን ለመቀነስ ክትባቱን ላልተከተቡ በሚውለው ክፍሎች ላይ የማህበራዊ ርቀትን መስፈርት እና የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል መጠቀም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ።

## የንግድ ስራዎች እና ድርጅቶች የትኛውን የንፅህና አጠባበቅ መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ መቀጠል ይኖርባቸዋል?

የሲዲሲ የንፅህና መጠበቂያ ወይም የፀረ፡ተባይ ማጥፊያ (ዲስእንፌክታንት) መመሪያ  የኮቪድ-19ን በሽታ እና ተላላፊ በሽታዎችን የማሰራጨት አደጋን ለመቀነስ ጠቃሚ ነው። በተደጋጋሚ በእጅ የሚነኩ ስፍራዎችን አዘውትሮ ማድዳት ፣ ሰራተኞች በተደጋጋሚ እጆቻቸውን እንዲታጠቡ ማበረታታት፣ ለደንበኞች የእጅ ማፅጃ ማቅረብ፤ በማስነጠስ እና በሳል የሚወጡ ጠብታዎችን የሚከለክል መሰናከያ (ፕሌክሲግላስ) ወይም ሌላ አይነት መከላከያዎች መጠቀም የደንበኞችን እና የሠራተኞችን ህመም ለመቀነስ ይጠቅማል። በስራ ቦታ የኮቪድ-19 በሽታን የመተላለፍ አደጋን ስለመቀነስ በተመለከተ በዋሽንግተን የስራና ኢንደስትሪ መምሪያ በሥራ ቦታ ላይ ከቪድ-19ን ለመከላከል የወጣውን መስፈርቶች እና መመሪያ  ድረ ገፅ ይመልከቱ።

## እዚህ ያልተዘረዘሩ ጥያቄዎች አሉት?

ለተጨማሪ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት እባክዎ የዋሽንግተን ግዛት የጤና መምሪያ ስለ እንደገና መከፈት  እና የፊት መሸፈኛ ጭንብል መልበስ  ተደጋግሞ የሚነሱ ጥያቄዎችን መልስ የሚሰጥበት ድረ-ገፅ ላይ ይመልከቱ።